ግብርና ሚኒስቴር
MINISTRY OF AGRICULTURE

# ‘የግብርና ምርት ውል’ ረቂቅ አዋጅ አዘገጃጀት መግለጫ እና በሀገር አቀፍ ደረጃ የማውጣት አስፈላጊነት ሰነድ

**መስከረም 2012 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**

# ክፍል አንድ

## ‘የግብርና ምርት ውል’ አዋጅን ለማውጣት የቀረበ መግለጫ፣

### 1. መግቢያ

የወጪ ንግድ አስተባባሪ ብሔራዊ ኮሚቴ መጋቢት 14 ቀን 2009 ዓ/ም ባካሄደው ስብሰባ " የአውት ግሮዎረስና ኮንትራት እርሻ በሕግ ማዕቀፍ የተደገፉ ባለመሆኑ የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ በሚያቀርበው ጥናት መሠረት የሕግ ማዕቀፍ በማዘጋጀት አቅም ያላቸውን ኩባንያዎች ፍላጎት ካላቸው አርሶ አደሮችና ማህበራት ጋር የማስተሳሰሩ ስራ ትኩረት ተሰጥቶት እንዲከናወን " መመሪያ ሰጥቷል፡፡ በተሰጠው መመሪያ መሠረት ጥናት ተካሂዶ በጥናቱ ምክረ ሀሳብ መሰረት “የግብርና ምርት ውል” ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቷል፡፡

ግብርና በኢትዮጵያ የልማት ፖሊሲዎች እና ስትራቴጅዎች ልዩ ቦታ የያዘ ዘርፍ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ከግብርና መር ኢንዱስትራያላይዜሽን ፖሊሲ እስከ እድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ሁሉም የሀገሪቱ የልማት ፖሊሲዎች ገጠርንና ግብርናን ማዕከል ያደረጉ ናቸው፡፡ በተለይም የሁለተኛው እድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ግብርናን መሠረት አድርጎ በአጠቃላይ ኢኮኖሚው ላይ መዋቅራዊ ለውጥ በማምጣት እ.ኤ.አ በ 2025 ኢትዮጵያን መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ ለማሰለፍ ያለመ ሰፊ የልማት አጀንዳ ነው፡፡ የታቀደውን አጠቃላይ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣትም አነስተኛ ይዞታ ባላቸው አርሶ/አርብቶ አደሮች ላይ የተመሠረተውን ግብርና ወደ ገበያ ተኮር ማሸጋገር እንደሚያስፈልግ የሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በግልፅ ያስቀምጣል፡፡ በዚህም ግብርናው አገራዊ የምግብ ፍላጎትን ከማሟላት ባሻገር በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ የሆኑ የኤክስፖርት ምርቶችን በብዛትና በጥራት በማቅረብ፣ ለኢንዱስትሪው ዘርፍ ጥሬ ዕቃ በማቅረብና እና ለኢንዱስትሪ ምርቶች ገበያን በመፍጠር ቁልፍ ሚና እንዲጫወት ይጠበቃል፡፡

ግብርናው የሚጠበቅበትን ሚና እንዲጫወት አንድ ቁልፍ ጉዳይ ለግብርና ምርት ግብይት አመቺ ሁኔታ መፍጠር መሆኑ በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ላይ በግልፅ ተመልክቷል፡፡ በዚህም የግብርና ምርቶችን ግብይት ሥርዐት ከምርት እስከ ወጭ ንግድ መዳረሻ ገበያ ድረስ ወጥና በተሟላ መልኩ በመገንባት ዘመናዊ የግብይት ስርዓት መፍጠር እንደሚያስፈልግ ግልፅ ነው፡፡

አርሶ/አርብቶ አደሩን ከእጅ ወደ አፍ ከሆነ አመራረት ሂደት ተላቆ የተሻለ ዋጋ ወዳላቸው ምርቶች ወደማምረት እንዲሸጋገር በማድረግ ከምርቱ የሚያገኘው ገቢ እንዲያድግ ማድረግ ለግብርናው ዘርፍ መዋቅራዊ ለውጥ ወሳኝ ነው፡፡ ይህንንም ለማድረግ የግብርና ምርትና ግብይት ስርዓቱ ከፍተኛ ሚና ሊጫዎት እንደሚችል በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፍርሜሽን ዕቅድ ላይ ተመልክቷል፡፡

ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ፤ የድህረ-ምርት ብክነትን ለመቀነስ እና አርሶ/አርብቶ አደሮችን ከአስተማማኝ ገዥዎች በማገናኘት ጠንካራ የገበያ ትስስር ለመፍጠር የግብርና ምርት ውልን መንግስት ሲያበረታታ ቆይቷል፡፡ እያበረታታም ይገኛል፡፡

የግብርና ምርት ውል ለተዋዋይ ወገኖች ከሚሰጠው ጥቅም ባለፈ ለግብርና ልማት ከፍተኛ አስተዋጾ ያደርጋል፡፡ ለአርሶ/አርብቶ አደሮች አዲስ ገበያ በመፍጠር ቴክኖሎጂና ክህሎትን በማስተላላፍ እንዲሁም የግብዐትና የብድር አቅርቦትን በማመቻቸት

ወዘተ የተሻለ ገቢ እንዲያገኙ ያግዛል፡፡የምርቱ ገዥዎችም በሚፈልጉት ጊዜ፣ መጠንና ጥራት የግብርና ምርቶችን በአስተማማኝ ሁኔታ እንዲያገኙ ይረዳል፡፡ በዚህም ለግብርናው መዋቅራዊ ለውጥ እና ለድህነት ቅነሳ የሚያበረክተው አስተዋጾ ከፍተኛ ነው፡ ፡

ውጤታማ የግብርና ምርት ውል እንዲኖር አጋዥ የሆኑ የሕግና ተቋማዊ ስርዓቶች ሊዘረጉለት ይገባል፡፡ በእርግጥ በአምራቹ/አርቢውና በገዢው መካከል የሚኖረው ግንኙነት የውል ግንኙነት እንደመሆኑ መደበኛው የውል ሕግ ግንኙነቱን ሊገዛ ይችላል፡፡ ይሁንና ጠቅላላ የውል ሕጎች የተወሰኑ በአምራቹ/አርቢውና በገዢው መካከል የሚኖሩ ግንኙነቶችን ሊገዙ ቢችሉም የግብርና ምርት ውል ልዩ ባህሪያትን ሙሉ በሙሉ ሊያስተናግዱ የሚችሉ አይደሉም፡፡ በተለይም አብዛኛው ግብርና አነስተኛ ይዞታ ባላቸው አርሶ/አርብቶ አደሮች በሚከናወንበት አገራችን ራሱን የቻለ ዝርዝር ሕግ መኖሩ ጠቀሜታው የላቀ ነው፡፡

2. <u>**የግብርና ምርት ውልን የተመለከተ የተለየ ሕግ አስፈላጊነትን የሚያጎሉ የተለያዩ ምክንያቶች በተደረገው ጥናት የተለዩ ሲሆን ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፤**</u>

1ኛ. የግብርና ምርት ውል ተዋናዮችና ባለድርሻ አካላት በርካታ መሆናቸው፤ እንደማንኛውም የውል ግንኙነት የግብርና ምርት ውል በዋናነት ተዋዋይ ወገኖችን የሚመለከት ቢሆንም ከተዋዋይ ወገኖች ባሻገር የተለያዩ ባለድርሻ አካላትንም የሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡ ለምሳሌም መንግስት የውል ግኑኝነቱን ለምርትና ምርታማነት መጨመርና ለግብርና እድገት አስተዋጽዎ እንዲያደርግ ይፈልጋል፡፡ በተጨማሪም የሕብረት ሥራ ማህበራት የአባላቶቻቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ ይችሉ ዘንድ የራሳቸውን ሚና መጫዎት ይፈልጋሉ፡፡ በመሆኑም የግብርና ምርት ውል ከተዋዋይ ወገኖች ባለፈ የተለያዩ የባለድርሻ አካላትን ጥቅሞችና ፍላጎቶች የሚመለከት በመሆኑ ይህንኑ ያገናዘበ ራሱን የቻለ ሕግ ያስፈልገዋል፡፡

2ኛ. በተዋዋይ ወገኖች መካከል የመደራደር ዐቅም ልዩነት መኖር፤ በተለያዩ ምክንያቶች ተዋዋይ ወገኖች እኩል የመደራደር ዐቅም ላይኖራቸው ይችላል፡፡ በተለይም አነስተኛ ይዞታ ያላቸው አርሶ/አርብቶ አደሮች ከታላላቅ ገዢዎች ጋር እኩል የሆነ የመደራደር ዐቅም እንደማይኖራቸው ግልፅ ነው፡፡ የግብርና ምርት ውልን የተመለከተ እራሱን የቻለ ሕግ መኖር ይህንን የዐቅም ልዩነት በተወሰነ ደረጃ እንዲጠብ ያግዛል፡፡

3ኛ. የግብርና ምርት አመራረት ሂደት ለተለያዩ አደጋዎች የተጋለጠ መሆኑ፤ ለምሳሌም በአየር ንብረት መለዋወጥ፣ በበሽታ፣ ወዘተ ምክንያት በውሉ መሠረት መፈፀም የማይቻልባቸው ሁኔታዎች ሊፈጠሩ ይችላሉ፡፡ በዚህም የተነሳ በተዋዋይ ወገኖች መካከል አለመግባባቶች ሊፈጠሩ ይችላሉ፡፡ የግብርና ምርት ውልን የተመለከተ የተለየ ሕግ የግብርና ምርት ልዩ ባህሪያትን ግምት ዉስጥ ያስገባ አለመግባባቶችን የመፍቻ መንገዶች በማመቻቸት በተዋዋይ ወገኖች መሀከል ፍትሀዊ ግንኙነት እንዲኖር እና የተረጋጋ የግብርና ምርትና ግብይት እንዲኖር ያስችላል፡፡

4ኛ. የግብርና ምርት ውል እንዲስፋፋ፣ እንዲበረታታ እና ለግብርና ምርት ዕድገት ዋነኛ መሣሪያ እንዲሆን ተቋማዊ ስርዓት እንዲኖረዉ ያስፈልጋል፤ በመሆኑም እራሱን የቻለ ሕግ የግብርና ምርት ውልን በስፋት ለማስተዋወቅ፣ ለማስፋፋትና ለማስተባበር የሚያስችል ተቋማዊ ስርዓትን ለመሰየም ያስችላል፡፡

5ኛ . ወጥ የሆነ የግብርና ምርት ውል አሰራር እንዲኖር ያስችላል፤ አሁን በተግባር የሚታየው ወጥነት የሌለውና የተዘበራረቀ አሰራር ነው፡፡ የግብርና ምርት ውልን በወጥነት የሚገዛ ሕግ ባለመኖሩ ተወዋይ ወገኖች በመሰላቸው የውል ግንኙነቶችን

ሲያከናውኑ ይታያል፡፡ ይህም አሰራር ለውሎች አፈፃፃም አሰቸጋሪ እና ለአለመግባባቶች በር ሲከፍት ይታያል፡፡ እራሱን የቻለ የግብርና ምርት ውል ሕግ መኖር ወጥ የሆነ አሰራርን በመዘርጋት ይህንን ችግር ይፈታል፡፡

በመግቢያው ላይ በተጠቀሰው ጥናት ምክረሀሳብና በጥናቱ መሰረት በተዘጋጀው የግብርና ምርት ውል ረቂቅ አዋጅ ላይ በህዳር ወር 2010 ዓ.ም በተከታታይ በተዘጋጁ መድረኮች የፌደራልና የክልል ባለድርሻ አካላት አስተያየት እንዲሰጡበት የተደረገ ሲሆን በማስከተልም ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸው የፌደራል መስሪያ ቤቶች (በቀድሞ አጠራራቸው) ማለትም፤ የግብርናና የእንስሳት ሀብት ሚኒስቴር፤የንግድ ሚኒስቴር፤የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፤የሆርቲካልቸርና ግብርና ኢንቨስትመንት ባለሥልጣን፤የቡናና ሻይ ባለስልጣን፤የምርት ገበያ ባለስልጣን እና የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ለበላይ ሀላፊዎች ረቂቅ አዋጁ ግንቦት 29 ቀን 2010 ዓ.ም ቀርቦ ተጨማሪ አስተያየት ተሰጥቶበት ዳብሯል።

በየደረጃው የዳበረዉ ረቂቅ አዋጅ የካቲት 30 ቀን 2011 ዓ.ም በተዘጋጀ የማጠቃለያ መድረክ የፌደራልና የክልል ባለድርሻ አካላት አስተያየት እንዲሰጡበት ተደርጓል ፡፡

ረቂቅ አዋጁ በፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ሁለት ዙር አስተያየት የተሰጠበት ሲሆን በፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የተሰጠው አስተያየት በረቂቅ አዋጁ እንዲካተት ተደርጓል ፡፡

ለማጠቃለል የግብርና ምርት ውል ለግብርናው እድገት እና የአርሶ/አርብቶ አደሮችን ኑሮ ለማሻሻል የሚያበረክተውን ከፍተኛ አስተዋፅዖ እውን ለማድረግ ይቻል ዘንድ ዘርፉን የሚመራ፣የሚያስፋፋ እና የሚያሳልጥ ሀገር አቀፍ የሕግ ማዕቀፍ በማስፈለጉ፤ በጥናት ላይ ተመስርቶ፤ የሌሎችን ሀገራት ውጤታማ ልምድ በመውሰድና ከሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ በየደረጃው ያሉ ባለድርሻ አካላትን አስተያቶች አካቶ የተዘጋጀው የግብርና ምርት ውል ረቂቅ አዋጅ ቀርቧል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

### <u>'የግብርና ምርት ውል' አዋጅ በሀገር አቀፍ ደረጃ የማውጣት አስፈላጊነት</u>

የግብርና ምርት ውል አዋጅ በሀገር አቀፍ ደረጃ ማውጣት የሚያስፈልግበት ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

1. የተቀናጀ የግብርና ምርት ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች የሚፈለገው ምርት ዓይነት፣ በጥራት፣ በሚፈለገው መጠንና ጊዜ ለማግኘት ከአልሚ አነስተኛ አምራች አርሶ/አርብቶ አደሮችና ባለሃብቶች በውል ላይ የተመሰረተ የምርት እና ግብይት ግንኙነት መፍጠር የሚያስችል የተሟላ ሀገር አቀፍ የህግ ማዕቀፍ አለመኖሩ፤
2. ሰፋፊ እርሻዎች በዙሪያቸው ካሉ አነስተኛ ይዞታ ካላቸው አርሶ/አርብቶ አደሮች በልማትና ግብይት ተሳስረው ኢኮኖሚው በተለይም ገበያ የሚፈልገውን ምርት በማምረት የጋራ ተጠቃሚነትን ለማሳደግ የሚያስችል የተሟላ ሀገር አቀፍ የህግ ማእቀፍ አለመኖሩ፤
3. ገበያ መር የግብርና ልማት ለማረጋገጥና አነስተኛ ይዞታ ያላቸው አርሶ/አርብቶአደሮች የአመራረት ሥርዓት በመቀየር ከፍጆታ ማምረት ከገበያ የሚፈለግና የተሻለ ዋጋ የሚያስገኝ ምርት ወደ ማምረት ለማሸጋገር በውል ላይ የተመሰረተ የልማትና ግብይት ትስስር ከሰፋፊ እርሻዎች፣የግብርና ምርት ከሚቀበሉ ኢንዱስትሪዎች፣ ከላኪዎችና የገበያ ማዕከላት ጋር ማስተሳሰር ይጠይቃል፡፡ ከዚህ አኳያ የአገር ውስጥ ባለሃብትም ይሁን ዓለምአቀፍ ኩባንያዎችን በመሳብ ክልል

ተሻጋሪ የሆነ እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ ስለሚያስገድድና ዓለም አቀፍ ኩባንያዎችም ይህኑን በሁሉም የአገሪቱ ክልሎች የሚሰራ የግብርና ምርት ውል የተሟላ የህግ ማዕቀፍ (ይህንኑ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚውጣ ህግን መሰረት በማድረግ በክልሎች የሚወጣ ህግ) ቅድመ ሁኔታ አድርገው እየጠይቁ በመሆኑ፤ በተለይም የምርጥ ዘር አምራች ኩባንያዎች ፤

4. *የተቀናጀ የግብርና ምርት ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች ልማት አገራዊ ይዘት ያለው በመሆኑ ከውጭ ጋር የተያያዘ ካፒታል እና የቴክኖሎጂ አቅም የሚጠይቅ የውጭ ባላሃብቶች በዘርፉ እንዲሰማሩ እየተደረገ በመሆኑ ይህም በሁሉም የአገሪቱ ክልሎች የሚሰራ የግብርና ምርት ውል የተሟላ የህግ ማዕቀፍ ስለሚጠይቅ ፤*
5. *የግብርና ምርት ውል በተመከተ ህግ የማውጣት ስልጣን የክልሎች ብቻ ነው ከተባለ እያዳንድ ክልል የሚያወጣ ህግ የሚገዛው አምራችና አስመራች በክልሉ ውስጥ ሆነው የሚደረግን የግብርና ምርት ውል ነው ፡፡ አምራች አንድ ክልል ሆኖ አስመራች ሌላ ክልል በሚሆንበት ጊዜ ወይም አስመራች አለም ዐቀፍ ገዥ ሲሆን የግብርና ምርት ውላቸውን የሚገዛ በሀገር አቀፍ ደረጃ የወጣየግብርና ምርት ውል አዋጅ መኖሩ የግድ ነው ፤*
6. *ከላይ እንደተገለፀው የግብርና ምርት ውል እንዲስፋፋ፣ እንዲበረታታ እና ለግብርና ምርት ዕድገት ዋነኛ መሣሪያ እንዲሆን ተቋማዊ ስርዓት እንዲኖረዉ ያስፈልጋል፡፡ እራሱን የቻለ የግብርና ምርት ውል አዋጅ በሀገር አቀፍ ደረጃ ማውጣት የግብርና ምርት ውልን በስፋት ለማስተዋወቅ፣ ለማስፋፋትና ለማስተባበር የሚያስችል ተቋማዊ ስርዓትን በሀገር አቀፍ ደረጃ ለመሰየም ያስችላል፡፡ የግብርና ምርት ውል አዋጅ በክልል ደረጃ ብቻ ይውጣ ከተባለ ግን በሃገራቀፍ ደረጃ የግብርና ምርት ውልን በስፋት ለማስተዋወቅ፣ ለማስፋፋትና ለማስተባበር የሚያስችል ተቋማዊ ስርዓትን በሀገር አቀፍ ደረጃ ለመሰየም የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ ስለማይኖር ይህም አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ በመፍጠር አገራዊ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ትስስርን እውን እንዳይሆን አሉታዊ ተጽዕኖ ስላለው ፤*
7. *የግብርና ምርት ውልን በወጥነት የሚገዛ ሕግ ባለመኖሩ አሁን በተግባር የሚታየው ወጥነት የሌለውና የተዘበራራቀ አሰራር ነው፡፡ ይህም አሰራር ለውሎች አፈፃፀም አስቸጋሪ እና ለአለመግባባቶች በር ሲከፍት ይታያል፡፡ ይህን ችግር የግብርና ምርት ውል አዋጅ በክልል ደረጃ ብቻ ይውጣ ቢባል በወሳኝ መልኩ አይፈታም፡፡ ችግሩ ትርጉም ባለው ደረጃ የሚፈታው የግብርና ምርት ውል አዋጅ በሀገር አቀፍ ደረጃ ተደንግጎ ክልሎችም በፌዴራል የሚወጣውን አዋጅ መሰረት በማድረግ የራሳቸው አዋጅ ሲያወጡ ነው ፡፡*
8. *የግብርና ምርት ውልን የተመለከተ የተለየ ሕግ የሚያስፈልገው የግብርና ምርት ልዩ ባህሪያትን ግምት ዉስጥ ያስገባ አለመግባባቶችን የመፍቻ መንገዶች በማመቻቸት በተዋዋይ ወገኖች መሀከል ፍትሀዊ ግንኙነት እንዲኖር እና የተረጋጋ የግብርና ምርትና ግብይት እንዲኖር ስለሚያስችል እንደሆነ ከላይ ተገልጿል ፡፡ በብሔራዊ ደረጃ የግብርና ምርት ውል አዋጅ ሳይወጣ እያንዳንዱ ክልል ያውጣ ቢባል ግን የክልሎች ሕግ በተዋዋይ ወገኖች መካከል አለመግባባቶች ሲፈጠር የሚፈቱበትን መንገዶች የሚያስቀምጡዋቸው ድንጋጌዎች የተለያዩ ሊሆኑ ስለሚችሉ ውጤቱም ከክልል ክልል የተለያየ አለመግባባቶችን የመፍቻ መንገዶች ሊሆን ስለሚችል ይህ መሆኑ ደግሞ ዜጎችን በእኩል አይን ያለማየት አላስፈላጊ ውጤት የሚኖረው ብቻ ሳየሆን በተዋዋይ ወገኖች መሀከል ፍትሀዊ ግንኙነት እንዳይኖር እና የተረጋጋ የግብርና ምርትና ግብይት በሀገር አቀፍ ደረጃ እንዳይሠፍን ያደርጋል፡፡*

*የግብርና ምርት ውል አዋጅ በሀገር አቀፍ ደረጃ እንዲወጣ ከተደረገ ግን በሁሉም የአገሪቱ ክልሎች የሚሰራ አለመግባባቶችን የመፍቻ መንገዶች መደንገግ ስለሚያስችል በተዋዋይ ወገኖች መሀከል ፍትሀዊ ግንኙነት እንዲኖር*

*እና የተረጋጋ የግብርና ምርትና ግብይት በሁሉም የአገሪቱ ክልሎች በሀገር አቀፍ ደረጃ እንዲሰፍን ለማድረግ ስለሚረዳ ይህም አንድ የኢኮኖሚና ፖለቲካ ማህበረሰብ በመፍጠር አገራዊ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ትስስርን ለማምጣት አስተዋጾው ከፍተኛ ነው ::*

ለማጠቃለል ግብርናን ለማዘመንም ሆነ ከኢንዱስትሪ ጋር ያለውን ትስስር ለማፋጠን ብሎም ሀገራዊ የማህበራዊ እና የኢኮኖሚያዊ ትስስርን ለመፍጠር እንዲቻል (ክልሎች የፌዴራሉን አዋጅ መሰረት በማድረግ የራሳቸው አዋጅ የማውጣት ሥልጣናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ) ወጥነት ያለውና ሀገር አቀፍ የግብርና ምርት ውልን አዋጅ ማውጣት አስፈላጊ መሆኑን የግብርና ሚኒስቴር አምኖበታል፡፡